

# ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት እስከ ምረቃ፡- የቤተሰብ የፖሊሲ መመሪያ

በትምህርት ቤት መገኘት

ሥነ-ሥርዓት

ውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል
ወደ ክፍል መሸጋገር

ውጤት እና ውጤትን ማሻሻል

ምረቃ

የትምህርት ዓመት 2019-2020

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

የተወደዳችሁ የዲሲፒኤስ (DCPS) ቤተሰቦች፤

በዲሲ የህዝብ ት/ቤቶች (DCPS), ተማሪዎች የላቀ ደረጃ የሚደርሱት ቤተሰቦች፤ አስተማሪዎች፤ የትምህርት ቤት አባላት፤ እና የማህበረሰቡ አባላት በጋራ በመስራት ስኬታማነታቸውን ሲደግፉ መሆኑን እናውቃለን። እያንዳንዱ ተማሪ መወደዱን፤ መፈተኑን እና አመርቂ በሆነው ከተማችን ውስጥ ያለውን እድገት እና እድል ለመጠቀም መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ከእርስዎ ጋር በጋራ ለመስራት ቁርጠኛ ነን።

*ከቅድመ-መዋዕለ ህጻናት እስከ ምረቃ (Pre-K to Graduation): የፖሊሲ መምሪያ ለቤተሰቦች (A Policy Guide for Families) ተማሪዎቻችን ማሟላት ስለሚጠበቅባቸው መስፈርቶች በግልጽ ሁኔታ የማስቀመጥ እና በዚህ የስኬት መንገዳቸውም ዲሲፒኤስ* (DCPS) *ምን ምን ድጋፎች እንደሚያደርግ ማሳወቅ ላይ ያለመ ነው።* ይህ መምሪያ በትምህርት ላይ መገኘትን፤ ሥነ-ሥርዓትን፤ና ውጤቶችን እና ከክፍል ወደ ክፍል ሽግግሮችን፤ ውጤት ማሻሻሎችን፤ እና ምረቃ የመሳሰሉትን ርዕሶች ጨምሮ በተደጋጋሚ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ተቀባይነት ያላቸውን ከትምህርት መቅረቶች፤ የማለፍ እና የመመረቅ መስፈርቶችን፤ ወይም ተማሪዎች እንዴት ውጤታቸውን ማሻሻል እንደሚችሉ ጥያቄዎች ካሉዎት በዚህ መመሪያ ውስጥ ሌሎችንም ጨምሮ ያገኟቸዋል።

ተማሪዎ ስኬታማ ለመሆን ስለሚከተሏቸው ቅደም ተከተሎች እና በትምህርት ጉዞአቸው ትምህርት ቤታቸው ስለሚያደርግላቸው ድጋፎች እንዲያውቁ ይህንን መረጃ ከተማሪዎ ጋር እንዲወያዩ አበረታታለሁ። አስተማሪዎቻችን እና የትምህርት ቤቱ አባላት የተማሪዎን ስኬታማነት ለመደገፍ አብረንዎት ለመስራት ጓጉተዋል። በጋራ በመሆን እያንዳንዱ ተማሪ ለኮሌጅ፤ ለስራ አንድ ለኑሮ መዘጋጀቱን እርግጠኛ እንሆናለን።

በትብብር፤



ሌዊስ ዲ ፈረቢ (Lewis D. Ferebee, Ed.D)
ቻንስለር (Chancellor)
ዲሲ የህዝብ ት/ቤቶች (DC Public Schools)

## ማውጫ

**በትምህርት ቤት መገኘት ...... 3**
ልጄ ከትምህርት ቤት ቀርቷል/ቀርታለች፡፡ የትኞቹ ምክንያቶች ለመቅረት “ተቀባይነት” አላቸው፣ ለትምህርት ቤቱስ እንዴት ነው የማሳውቀው? ...... 3
ልጄ በዲሲፒኤአስ (DCPS) ድጋፍ በተዘጋጀ ተግባር ወይም በአትሌቲክስ ዝግጅት ምክንያት ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጪ ይሆናል/ትሆናለች፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ነውን? ...... 4
ልጄ ከዲሲፒኤአስ (DCPS) ጋር ያልተገናኘ ትምህርታዊ ዝግጅት በትምህርት ቀን አለው/አላት፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ነውን? ...... 4
ልጄ ምክንያቱ ተቀባይነት የሌለው በርካታ ቀሪዎች ቢኖሩት ምን ይከሰታል? ...... 5
ልጄ በተከታታይ ከ20 ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ ምን ይከተላል? ...... 5
በቂ ባልሆነ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት በልጄ ውጤት እና ወደ ቀጣዩ ክፍል በመዘዋወር ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል? ...... 5
ልጄ ከባድ የጤና ችግር ቢኖርበት እና ት/ቤት መከታተል የማይችል ቢሆንስ? ...... 5
ልጄ ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ሲሆን/ስትሆን አስገዳጅ የትምህርት ቤት እድሜ ላይ አይደለም/አይደለችም፡፡ ትምህርት ቤት መገኘትን በሚመለከት ማወቅ የሚያስፈልገው ምንድነው? ...... 6
ልጄ ከ6-12ኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ/ና ቢያረፍድ/ብታረፍድ፣ እርፋጅ ተደርጎ/ተደርጋ የምትቆጠረው መቼ ነው? ...... 6
በትምህርት ቤት ስለመገኘት የሚገልጸውን ፖሊሲ በሚመለከት በይበልጥ ማወቅ የምችለው ከየት ነው? ...... 6
**ሥነ-ሥርዓት ...... 7**
ከመዋዕለ-ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍል ያለ ልጄ ቢታገድ/ብትታገድ በእገዳው ቀናት ላይ ገደብ አለን? ...... 7
ልጄ ሊደርሰው በሚችለው ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ ቀናት ላይ የቀናቶቹን ብዛት በሚመለከት ገደብ አለ? ...... 7
በእግድ ሒደት ውስጥ የልጄ መብቶች ምን ምን ናቸው? ...... 8
እግድ በትምህርት ቤት በመገኘት ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድነው? ...... 8
የልጄን እግድ በተመለከተ የሚያሳስቡኝ ነገሮች አሉ፡፡ በልጄ እግድ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ስለምችልበት ቦታ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው የት ነው? ...... 9
**ውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል ስለመዘዋወር ...... 10**
ከመዋዕለ-ህጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያለ ልጄ ወደቀጣዩ የክፍል ደረጃ ለመሸጋገር ምን ማድረግ ያስፈልገዋል? ...... 10
በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ያለ ልጄ ወደቀጣዩ የክፍል ደረጃ ለመሸጋገር ምን ማድረግ ያስፈልገዋል? ...... 10
ልጄ የማለፊያውን መስፈርት ካላሟላ የበጋ ትምህርት መከታተል ይጠበቅበታል? ...... 10
የልጄን የትምህርት እድገት በሚመለከት እንዴት ማወቅ እችላለሁ? ...... 11
ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ውስጥ ልጄ ያመለጠውን/ጣትን የክፍል ስራ ማካካስ ይችላል/ትችላለች? ...... 11
ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የልጄ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት መቅረት በልጄ የትምህርት ውጤት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድነው? ...... 11
በልጄ ውጤቶች እና/ወይም የመድገም ውሳኔ ላይ ጥርጣሬዎች ቢኖሩኝ ይግባኝ የማልቱ ሂደት እንዴት ነው? ...... 11
**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውጤትን ማሻሻል ...... 13**
ልጄ ውጤት ማሻሻያ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ነው? ...... 13
ውጤትን ለማሻሻል ልጄ የት መመዝገብ ይችላል? ...... 13
ልጄ የውጤት ማሻሻያ ትምህርትን ሲከታተል በትምህርት ላይ የመገኘት መስፈርቶቹ ምንድናቸው? ...... 13
ምን አይነት ውጤቶች ናቸው ልጄ የውጤት ማሻሻያ ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ማጠናቀቁን የሚያሳዩት? ...... 13
**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምረቃ ...... 14**
የ ዲሲፒኤስ (DCPS) የምረቃ መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ...... 14
ከሌላ ት/ቤት የተገኙ ተላላፊ ውጤቶች እንዴት ነው የሚገመገሙት ...... 15
ለልጄ አማካይ የውጤት ነጥቦች (GPAs) እንዴት ነው የሚሰሉት? ...... 15
ልጄ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰዓትን የት ማጠናቀቅ ይችላል? ...... 15
ልጄ ለመመረቅ፤ ለኮሌጅ፤ እና ለስራ የሚያደርጋቸውን ሂደቶች እንዴት ማወቅ እችላለሁ? ...... 16
**የመቅረትን ምክንያት ማብራሪያ መልዕክት ...... 17**
**የይግባኝ ቅጽ ...... 18**

# በትምህርት ቤት መገኘት

## ምልከታ

በDCPS እያንዳንዱ ተማሪ ፍቅር እንደሚወደድ እንዲሰማው፣ የሚሰጠው ትምህርት የሚፈትነው እንዲሆን እና በኅብረተሰቡ ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ለማምጣት እንዲሁም በሕይወቱ ስኬታማ እንዲሆን እንፈልጋለን። ይህንን ለማሳካት እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል እና እያንዳንዱ ቀን ወሳኝ ነው። በትምህርት ዓለም እና በሕይወት በእያንዳንዱ ቀን በትምህርት ቤት መገኘት እና መማር እጅግ ወሳኝ ነው። በእያንዳንዱ የዲ DCPS ትምህርት ቤት፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ በየዕለቱ በትምህርት ቤት ስለመገኘቱ ቁጥጥር ይደረጋል።

- ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እና ወደ ክፍል ሠዓት ጠብቀው መገኘታቸው።
- ተማሪዎች ይዘው መመጣት የሚገባቸውን ማቴሪያሎች ይዘው መምጣታቸው።
- ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ከቀሩ፣ እነርሱ እና ቤተሰቦቻቸው ከትምህርት ቤት የቀሩበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወሻ ይዘው መምጣት እና ማካካሻ የቤት ሥራ እንዲሰጣቸው መጠየቅ አለባቸው።

ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጣ/እንዳትመጣ የሚያደርጉ አስቸጋሪ ነገሮች ካሉ እነርሱን ለማስቀረት እገዛ ለማግኘት የልጅዎን መምህር ወይም ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ (ለምሳሌ፣ የደህንነት ጉዳይ ወይም የትራንስፖርት አለመኖር)።

## ልጄ ከትምህርት ቤት ቀርቷል/ቀርታለች፡፡ የትኞቹ ምክንያቶች ለመቅረት "ተቀባይነት" አላቸው፣ ለትምህርት ቤቱስ እንዴት ነው የማሳውቀው?

ከትምህርት ቤት መቅረት፣ በየትኛውም የቀኑ የትምህርት ጊዜ በቂ ምክንያት ሳይኖር አለመገኘት ያለ ምክንያት መቅረት ተብሎ ይመዘገባል፡፡ ከዚህ በማስከተል የተዘረዘሩት ምክንያቶች ከትምህርት ቤት ለመቅረት **ተቀባይነት ያላቸው** ተብለው ይቆጠራሉ፡-

- የተማሪው/ዋ መታመም (በአንድ የትምህርት ተርም አንድ ተማሪ ለአምስት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ቀናት የቀረ/ች እንደሆነ በሐኪም የተሰጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት)፤
- የወላጅነት ኃላፊነት ያላቸው ተማሪዎች መታመም (ተማሪው/ዋ ለአምስት ቀናት ወይም ከዚያ በላይ በአንድ ተርም የቀረ/ች እንደሆነ ለተማሪው ልጅ በሐኪም የተሰጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት)፤
- የተማሪ አካላዊ ወይም የጥርስ ሕክምና ቀጠሮ፤
- የተማሪው/ዋ የቅርብ ቤተሰብ አባል ሞት፤
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ባለስልጣናት በኳረንቲን፣ በተላላፊ በሽታ፣ በኢንፌክሽን፣ በተባይ መባዛት፣ ወይም ሌሎች በጤና ምክንያቶች ከተማሪ መለየትን በሚጠይቁ ሁኔታዎች ምክንያት በተሰጠ የመለየት ትዕዛዝ፤
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ባለስልጣናት በኳረንቲን፣ በተላላፊ በሽታ፣ በኢንፌክሽን፣ በተባይ መባዛት፣ ወይም ሌሎች በጤና ምክንያቶች ከተማሪ መለየትን በሚጠይቁ ሁኔታዎች ምክንያት በተሰጠ የመለየት ትዕዛዝ፤
- ሃይማኖታዊ በዓል ለማክበር፤
- ከሃይማኖታዊ በዓል ውጪ የሃይማኖታዊ ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ (በድምሩ እስከ አምስት ቀናት)፤
- ተማሪዎች በጦር ሠራዊት ያሉ ወላጆቻቸውን ከግዳጅ በፊት፣ በግዳጅ ወቅት ወይም ከግዳጅ በኋላ ለመጠየቅ፤
- ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች የኮሌጅ ጉብኝት ለማድረግ (በድምሩ እስከ ሶስት ቀናት)፤
- ከሕፃናት መዋያ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ጉብኝት (አንድ ቀን)፤
- ነፍሰ ጡር ለሆኑ ወይም ወላጅ ለሆኑ ተማሪዎች በሐኪም በሚሰጥ ትዕዛዝ እና ማናቸውም በሕግ በተቀመጡ ደንቦች መሠረት፤
- ቴክ አወር ዶውተርስ ኤንድ ሰንስ ቱ ወርክ ደይ (ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችንን ወደ ሥራ ቀን እንውሰድ)፤ እና
- በ DCPS የፀደቀ ድንገተኛ ወይም ሌላ ሁኔታ፡፡

ከትምህርት ቤት መቅረት ምክንያታዊ ነው ተብሎ እንዲቆጠር **ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሰ/ች በኋላ ባሉት አምስት (5) ቀናት ውስጥ በጽሑፍ የተሰጠ ማስረጃ በተማሪው/ዋ ወላጅ መቅረብ አለበት**፡፡ በአምስት (5) የትምህርት ቀናት ውስጥ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሲቀርብ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች የመቅረቱን ሁኔታ ተቀባይነት እንዳለው መመዝገብ አለባቸው፡፡

የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ የራሳቸውን ማስታወሻ መፃፍ ወይም ከዚህ ሰነድ መጨረሻ በተያያዘው የDCPS የቀሪ ምክንያት ማስታወሻ ቅጽ መሙላት ይችላሉ፡ ፡ በዚህ ማብራሪያ ውስጥ የሚከተሉት ማብራሪያዎች መካተት አለባቸው፡-

- የተማሪው/ዋ ስም
- የወላጅ/አሳዳጊ ስም
- የወላጅ/አሳዳጊ አድራሻ

- ለመቅረት ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተገለጸበት ማስታወሻ ቀን
- የቀሪ ቀን (ቀናት)
- ተማሪው/ዋ የቀረበት/ችበት ምክንያት

የቀረበትን ምክንያት በጽሁፍ ማቅረብን በሚመለከት ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት እባክዎ የልጅዎን ት/ቤት ያነጋግሩ።

አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ፡-

- ከትምህርት ቤት የቀረው/የቀረችው **በእያንዳንዱ ተርም በድምሩ እስከ አራት (4) ቀናት** በሚሆን ጊዜ፣ በወላጅ በጽሑፍ የሚሰጥ ማብራሪያ ለመቅረቱ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መልኩ ተማሪው/ዋ የቀረ/ች እንደሆነ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ውስጥ የሚካተት ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፤
- **በእያንዳንዱ ተርም በድምሩ ለአምስት (5) ወይም ከዚያ በላይ** የቀረ/ች እንደሆነ ለቀሪው ምክንያት ለማቅረብ ተጨማሪ ሰነዶች ያስፈልጋሉ፡፡ የተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ልጅ ከትምህርት ቤት የቀረበትን/የቀረችበትን ምክንያት የሚያብራራው ጽሑፍ በሐኪም ወይም በሚመለከተው ኤጀንሲ ሠራተኛ በሚጻፍበት ጊዜ፣ ማስረጃው በሐኪሙ ተቋም/በኤጀንሲው የደብዳቤ መጻፊያ ወረቀት ተዘጋጅቶ በሚመለከተው ኃላፊ ሊፈረምበት ይገባል፡፡ ያስታውሱ፡-
    - o በአካላዊ ወይም በጥርስ ጤና ምክንያት ከትምህርት ቤት የተቀረ እንደሆነ፣ ማስረጃው መቅረብ ያለበት በሐኪሙ/በጥርስ ሕክምና ባለሙያው የደብዳቤ መጻፊያ ወረቀት ወይም ቅጽ ሊሆን ይገባል፤ እንዲሁም
    - o ተማሪው/ዋ በፍርድ ቤት መገኘት ያለበት በመሆኑ/ኗ ምክንያት የቀረ/ች እንደሆነ፣ ለመቅረት ምክንያት የሆነው ይህ ምክንያት በፍርድ ቤት በተሰጠ ሰነድ መረጋገጥ እና ተማሪው/ዋ በፍርድ ቤት የተገኘበትን/ችበትን ቀናት ሁሉ የያዘ መሆን አለበት፡፡
    - o የቀብር ፕሮግራም በተማሪው የቅርብ ቤተሰብ ሞት ምክንያት ከትምህርት ቤት ለመቅረት አግባብነት እንዳለው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡

## ልጄ በዲሲፒኤስ (DCPS) ድጋፍ በተዘጋጀ ተግባር ወይም በአትሌቲክስ ዝግጅት ምክንያት ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጪ ይሆናል/ትሆናለች፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ነውን?

አዎ፡፡ በዲሲፒኤስ (DCPS) በተዘጋጁ ዝግጅቶች፣ በመስክ ጉብኝቶች ወይም በመደበኛ የትምህርት ቀን ለትምህርት ወደ ውጪ አገር መጓዝ ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት እንደተገኘ/ች ይቆጠራል፡፡ በDCPS ስፖንሰር በተደረጉ የአትሌቲክስ ዝግጅቶች በመደበኛ የትምህርት ሠዓታት መሳተፍ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ነው፡፡ በማንኛውም የአትሌቲክስ ሙከራ፣ ዝግጅት፣ ግጥሚያ ወይም ጨዋታ ላይ ለመሳተፍ ተማሪው/ዋ በዚያው ቀን በትምህርት የትምህርት ቀን በትምህርት ቤት መገኘት እንዳለበት/ባት ማወቅ ይገባል፡፡ ይህም ማለት ተማሪው/ዋ ተቀባይነት ባለው ምክንያት የቀረ/ች ካልሆነ ነው፡፡

## ልጄ ከዲሲፒኤስ (DCPS) ጋር ያልተገናኘ ትምህርታዊ ዝግጅት በትምህርት ቀን አለው/አላት፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ነውን?

በጠቅላላው ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ያልተካተተ ምክንያት ለምሳሌ ለረጅም ጊዜ ጉዞ ማድረግ ተቀባይነት የሌላቸው ምክንያቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ አንድ ተማሪ ወይም ወላጅ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ ያልተካተተ ጉዳይ ያጋጥማል ብለው ካሰቡ፣ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት በልዩ ሁኔታ ከትምህርት ቤት ለመቅረት ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ርዕሰ መምህሩ/ሯ ከትምህርት ኃላፊ (ኢንስትራክሽናል ሱፐርኢንቴንደንት) ጋር በመመካከር የቀረበው ከትምህርት ቤት የመቅረት ጥያቄ ተቀባይነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለውን ይወስናል፡፡

## ልጄ ምክንያቱ ተቀባይነት የሌለው በርካታ ቀሪዎች ቢኖሩት ምን ይከሰታል?

እድሜያቸው ለትምህርት ቤት የደረሰ ተማሪዎች (ትርጓሜውን ከታች ይመልከቱ) በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ በቂ ምክንያት ሳይኖር **በተደጋጋሚ ከትምህርት ቤት የቀሩ** እንደሆነ፣ ከDCPS፣ ከትምህርት ቤቱ እና/ወይም ከተማሪው/ዋ መምህር/ት የሚከተሉት ማሳወቂያዎች ይደርሳቸዋል፡-

- **የ1 ቀን ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** አንድ ተማሪ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት አንድ ቀን ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ ወላጆች ይጠየቃሉ፡፡
- **የ3 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ለወላጆች ተቀባይነት የሌለው ከትምህርት ቤት የመቅረት ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡
- **የ5 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ወላጆች ተቀባይነት የሌለው ከትምህርት ቤት የመቅረት ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ተርም ውስጥ ተማሪው/ዋ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ለ5 ቀናት የቀረ/ች እንደሆነ ተማሪው/ዋ እንዲህ ካለው ሁኔታ ጋር በተያያዘ የድጋፍ አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ማለትም ለአቴንዳንስ ስቱደንት ሰፖርት ቡድን ይላካል/ትላካለች፡፡
- **የ7 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ወላጆች ከከተማው ፖሊስ መምሪያ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡
- **የ10 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት (ተማሪው/ዋ ከፍተኛ የመቅረት ሪኮርድ እንዳለው ይቆጠራል)፡-**
  - እድሜያቸው ከ5 - 13 ዓመት ለሆነ ተማሪዎች DCPS የሕፃናት ቤተሰብ አገልግሎቶችን (CFSA) ያነጋግራል፣
  - እድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ ለሆነ ተማሪዎች፣ DCPS ተማሪውን/ዋን በአቴንዳንስ ስቱደንት ሰፖርት ክትትል እንዲደረግለት/እንዲደረግላት ይልካል፡፡
  - ከቤት ሥራ እና በትምህርት ቤት ከመገኘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የማስጠንቀቂያ ፖሊሲዎች በውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል የመተላለፍ ክፍል ይመልከቱ፡፡
- **የ15 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-**
  - እድሜያቸው ከ14-17 ዓመት ለሆነ ተማሪዎች DCPS ተማሪውን ወደ ፍርድ ቤት የማኅበራዊ አገልግሎቶች ክፍል ይልካል፡፡
  - ከቤት ሥራ እና በትምህርት ቤት ከመገኘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የማስጠንቀቂያ ፖሊሲዎች በውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል የመተላለፍ ክፍል ይመልከቱ፡፡
- **የ20 ተከታታይ ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት ለመልቀቅ ብቁ ይሆናል/ትሆናለች (ከትምህርት ቤት ለመልቀቅ ብቁ ስለሚያደርጉ ምክንያቶች ቀጣዩን ጥያቄ ይመልከቱ)፡፡
- **ከ30 ቀናት በላይ ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የወዳቂነት ውጤት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ (ለ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በመቅረት ምክንያት ስለመውደቅ መረጃ ለማግኘት የውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል ስለመዘዋወር የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ፡፡)

**ማስታወሻ፡- በዚህ የትምህርት ዓመት ከሴፕቴምበር 30 በፊት ዕድሜያቸው አምስት (5) ዓመት የሞላቸው ተማሪዎች ለትምህርት ቤት እድሜያቸው የደረሰ ተደርገው ይቆጠራሉ፤ እነርሱም ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ የሚያስፈልጋቸውን መስፈርት እስኪያሟሉ ወይም የ18 ዓመት ዕድሜ እስኪሞላቸው ድረስ በትምህርት ቤት በየዕለቱ መገኘት አለባቸው፡፡*

## ልጄ በተከታታይ ከ20 ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ ምን ይከተላል?

በትምህርት ቤት የተመዘገበ/ች ተማሪ በቂ ምክንያት ሳይኖር ለ20 ቀናት የቀረ/ች እንደሆነ ትምህርት ቤት ባለመገኘት ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዲወጡ ሊደረግ ይችላል፡፡ ይህ ደንብ ተፈጻሚነት ያለው ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ኢንባውንደሪ ወይም አውት ኦፍ ባውንደሪ መሆናቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ነው፡፡ ተማሪዎች ሁል ጊዜም ዳግም ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ በአካባቢያቸው ወደሚገኘው ትምህርት ቤት መመለስ የሚችሉ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ አውት ኦፍ ባውንደሪ ከሆነ በተጠባባቂ ዝርዝር የተመዘገቡ ተማሪዎች ከተስተናገዱ በኋላ እድሉ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

## በቂ ባልሆነ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት በልጄ ውጤት እና ወደ ቀጣዩ ክፍል በመዘዋወር ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል?

እባክዎን ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል ስለመዘዋወር የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ፡፡

## ልጄ ከባድ የጤና ችግር ቢኖርበት እና ት/ቤት መከታተል የማይችል ቢሆንስ?

የዲሲፒኤስ የቤት እና የሆስፒታል መመሪያ መርሃ-ግብር (DCPS Home and Hospital Instruction Program (HHIP) በጤና ምክንያት ለሁለት ሳምንት እና ከዚያ በላይ ተወስነው ለሚቆዩ ተማሪዎች ግላዊ የሆነ ባሉበት የማስተማሪያ ናሙና (individualized, blended-learning instructional model) ይሰጣል። የዲሲፒኤስ የቤት እና የሆስፒታል መመሪያ መርሃ-ግብር (HHIP) ከአገር አቀፍ ደረጃዎችን (Common Core State Standards) እንዲሁም ከዲሲፒኤስ አደረጃጀት እና ስፋትን (DCPS Scope and Sequence) በማቀናጀት የጤና ዕክል ያለባቸውን ተማሪዎች የትምህርት እና የተዛማጅ አገልግሎቶች ፍላጎቶች ያሟላል። የዲሲፒኤስ የቤት እና የሆስፒታል መመሪያ መርሃ-ግብር (HHIP) ቡድን ተማሪዎችን፤ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፤ የህክምና ባለሙያዎችን፤ እና ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ተማሪ ስኬታማ በሆነ መልኩ ወደ ተመዘገቡበት ት/ቤት ወይም የትምህርት ሁኔታ ስኬታማ በሆነ መልኩ የማሸጋገር አላማ ያለውን ቡድን ያካትታል።

## ልጄ ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ሲሆን/ስትሆን አስገዳጅ የትምህርት ቤት እድሜ ላይ አይደለም/አይደለችም፡፡ ትምህርት ቤት መገኘትን በሚመለከት ማወቅ የሚያስፈልገው ምንድነው?

በዚህ የትምህርት ዓመት በሴፕቴምበር 30 በፊት አምስት (5) ዓመት የሚሞላቸው ልጆች የትምህርት ቤት ዕድሜ ላይ የደረሱ ተማሪዎች ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን፣ እነርሱም ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ የተቀመጡትን መስፈርቶች እስኪያሟሉ ወይም የ18 ዓመት እድሜ እስኪሞላቸው ድረስ በየዕለቱ ትምህርት ቤት መገኘት አለባቸው፡፡ PK3 እና PK4 አስገዳጅ የትምህርት ደረጃዎች ባይሆኑ እንኳን፣ ከPK3 እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በትምህርት ቤት በመደበኛነት መገኘታቸው እጅግ ጠቃሚ ነው ብሎ DCPS አበክሮ ያምናል፡፡ የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ተማሪዎች በቂ ምክንያት ያላቸው እና በቂ ምክንያት ሳይኖር ከትምህርት ቤት መቅረትን በተመለከተ የተቀመጡት ደንቦች በእነርሱ ላይ በእኩል ደረጃ ተፈጻሚነት አላቸው፡-

- **የ1 ቀን ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** አንድ ተማሪ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት አንድ ቀን ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ ወላጆች/አሳዳጊዎች ይጠየቃሉ፡፡
- **የ3 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ወላጆች/አሳዳጊዎች ተቀባይነት የሌለው ከትምህርት ቤት የመቅረት ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡
- **የ5 ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** ወላጆች/አሳዳጊዎች ተቀባይነት የሌለው ከትምህርት ቤት የመቅረት ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ተርም ውስጥ ተማሪው/ዋ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ለ5 ቀናት የቀረ/ች እንደሆነ ተማሪው/ዋ እንዲህ ካለው ሁኔታ ጋር በተያያዘ የድጋፍ አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ማለትም ለአቴንዳንስ ስቱደንት ሰፖርት ቡድን ይላካል/ትላካለች፡፡ በተጨማሪም፣ ወደ ኧርሊ ቻይልድ ሁድ ትምህርት የቤተሰብ አገልግሎት ቡድን መላክ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡
- **የ20 ተከታታይ ቀናት ተቀባይነት የሌለው መቅረት፡-** አንድ/አንዲት የተመዘገበ/ች ተማሪ በቂ ምክንያት ሳይኖር ለ20 ተከታታይ ቀናት ከትምህርት ቤት የቀረ/ች እንደሆነ በትምህርት ቤት ባለመገኘት ምክንያት እንዲለቀቁ ሊደረግ እና ተማሪው/ዋ በክልሉ ውስጥ ቢሆን/ብትሆን እንኳን በተጠባባቂ ዝርዝር የተመዘገቡ ተማሪዎች ከተስተናገዱ በኋላ አገልግሎት እንዲያገኝ/እንድታገኝ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ልጄ ከ6-12ኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ/ና ቢያረፍድ/ብታረፍድ፣ አርፋጅ ተደርጐ/ተደርጋ የምትቆጠረው መቼ ነው?

ሰዓት ጠብቆ በትምህርት ክፍል መገኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ***የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ*** (ከ6-12ኛ ክፍል) በይፋ ትምህርት ከሚጀምርበት ሰዓት ከ5 ደቂቃ በላይ አርፍዶ/ዳ ወደ ክፍል የመጣ/ች እንደሆነ አርፋጅ ተደርጐ ይመዘገባል፡፡ ተማሪዎች በየትኛውም ሰዓት ቢደርሱ ወደ ክፍል እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ አርፍደው የሚመጡ ተማሪዎች ነጻ ሆነው ወደ ክፍል እንዲገቡ መምህራን የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ ያረፈደ ተማሪ ወደ ክፍል እንዳይገባ ማድረግ ትርጉም የለውም፡፡ አንድ ተማሪ የክፍሉን የተወሰነ ጊዜ ከተከታተለ በክፍል እንደተገኘ ነገር ግን አርፋጅ እንደሆነ ተደርጐ ይመዘገባል፡፡ ተማሪው/ዋ በተደጋጋሚ የሚያረፍድ/የምታረፍድ እንኳን ቢሆን ይህ ተደምሮ በቀሪነት አይመዘገብም፡፡ ተማሪዎች ለማርፈዳቸው የሚሰጣቸው ምላሽ ተገቢ እና ምክንያታዊ መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎች በማርፈዳቸው ምክንያት መታገድ የለባቸውም፡፡

*ማስታወሻ፡- በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ የአርፋጅ ተማሪዎች ፖሊሲ የለም፣ ለተጨማሪ መረጃ የልጅዎን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ፡፡*

## በትምህርት ቤት ስለመገኘት የሚገልጸውን ፖሊሲ በሚመለከት በይበልጥ ማወቅ የምችለው ከየት ነው?

ስለ DCPS በትምህርት ቤት የመገኘት አሠራር፣ ሒደቶች እና ፖሊሲዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ፡፡ በተጨማሪም በDCPS ድረ ገጽ https://dcps.dc.gov/attendance ወይም ደግሞ ሁሉም ቀን ዋጋ አለው (Every Day Counts! Taskforce) ድረ-ገጽ https://attendance.dc.gov/ ላይ መረጃ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡

# ሥነ-ሥርዓት

## ምልከታ

DCPS እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችሉት እድሎች እና ድጋፎች የሚያገኙበትን ከባቢ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል፡፡ ከዚህ ዓላማ አንጻር፣ DCPS መላውን ተማሪ የሚደግፍ የትምህርት ከባቢ ለመፍጠር ይሠራል፣ እያንዳንዱ ተማሪ አስደሳች እና ጠንካራ ትምህርታዊ ሒደት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይጥራል፡፡

## ልጄ በባሕርይ ምክንያት ከክፍል እንዲወጣ/እንድትወጣ እና እገዳ እንዲጣልበት/እንዲጣልባት መደረጉ ተገልፆልኛል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?

የአንድ ተማሪ ባሕርይ እና በትምህርት ቤቱ ከባቢ ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ተማሪው/ዋ ለተወሰነ ጊዜ ከክፍሉ/ሏ ርቆ/ርቃ እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግን አስፈላጊ ሊያደርግ ይችላል፡፡ መታገድ ማለት ተማሪው/ዋ በሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ከመደበኛ የትምህርት መርሐ ግብር ርቆ/ቃ እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ተማሪዎች በባሕርያቸው ሁኔታ ላይ በመመስረት በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ ሊጣልባቸው ይችላል፡፡ እገዳ ከተሰጠ በኋላ፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ሊመለሱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች ወላጆች ወደ ትምህርት ክፍል ከመመለስ በፊት ስብሰባ እንዲቀመጡ መጥራት አይችሉም፡፡

**ከትምህርት ቤት ውጪ ስለሚሆን መታገድ**

ተማሪዎች ሕገወጥ በሆነ፣ በትምህርት ቤት የመማር ማስተማር ሒደት ወይም በትምህርት ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ ረብሻ ሲፈጥሩ ወይም ንብረት ሲያወድሙ ወይም በራሳቸው ወይም በሌሎች ላይ ከፍተኛ የሚባል ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲታገዱ መደረግ አለባቸው፡፡ ከK-5 ላሉ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ እግድ የሚጣለው ለአንድ (1) እስከ አምስት (5) ቀናት ሲሆን ከ6-12ኛ ክፍሎች ከ1-10 ቀናት ይሆናል፡፡ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲታገዱ ከተደረገ፡-

- ወደ ትምህርት ቤቱ ሕንፃ ወይም ቅጥር ግቢ መግባት፣ ወይም
- በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ዝግጅቶች ወይም በተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አይችሉም፣

ከትምህርት ቤት ውጪ ለታገደ ለማንኛውም ተማሪ፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች፡-

- የተማሪውን መታገድ በDCPS የሪኮርድ ሲሲተም መመዝገብ (የተማሪ ባሕርይ መከታተያ)፣
- ከትምህርት ቤት መቅረትን በቂ ምክንያት እንዳለው (ከትምህርት ቤት ውጪ ለሚሆን እገዳ) በአስፐን ላይ መመዝገብ፣
- ተማሪዎች በእግድ ላይ ባሉበት ጊዜ የሚሠሩት የቤት ሥራ እና የትምህርት ማዕቀፍ መስጠት፣ እና
- ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ ያመለጧቸውን ፈተናዎች፣ ልዩ ፕሮጀክት ወይም የመጨረሻ ፈተና እንዲወስዱ ያደርጋሉ፡፡

## ከመዋዕለ-ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍል ያለ ልጄ ቢታገድ/ብትታገድ በእገዳው ቀናት ላይ ገደብ አለን?

አዎ። ከ2019-20 የትምህርት ዓመት ጀምሮ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ የተካሄደም ቢሆን ሆነ ብሎ በሌላ ሰው ላይ የአካል ወይም የስሜት ጉዳት ካላደረሰ፤ ለማድረስ ካልሞከረ ወይም ካላስፈራራ በስተቀር ከትምህርት ቤት ወጪ እገዳ አይደርሳቸውም።

## ልጄ ሊደርሰው በሚችለው ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ ቀናት ላይ የቀናቶቹን ብዛት በሚመለከት ገደብ አለ?

አዎ። ከ2018ቱ የተማሪዎች ፍትሃዊ ትምህርት ማግኘትን (Student Fair Access to School Amendment Act of 2018) በሚመለከት በተሻሻለው አንቀስ መሰረት ተማሪዎች ከዲሲ ትምህርት ቤቶች ታግደው ሊቆዩ በሚችሉባቸው ተከታታይ እና ድምር ቀናት ላይ ገደቦች አሉ፡፡

- ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 5ኛ (K-5) ያሉ ተማሪዎች በአንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ከአምስት (5) ተከታታይ ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ ታግደው ሊቆዩ አይችሉም፡፡*
- ከ6ኛ እስከ12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በአንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ከ10 ተከታታይ ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ ታግደው ሊቆዩ አይችሉም፡፡*
- ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) ላሉ ተማሪዎች ከ20 ድምር ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ እግድ ሊጣል አይችልም፤ ሆኖም ግን የተጣለ እንደሆነ ቻንስለሩ ከአማራጭ መፍትሔዎች ይልቅ ከ20 ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ ማገዱን አግባብነት ያለው መሆኑን በግለጽ ለተማሪው እና ለወላጅ በጽሑፍ ማብራሪያ መስጠት አለባቸው፤ በአማራጭነትም የተማሪው ባሕርይ ከትምህርት ቤት ወዲያውኑ እንዲወጣ ማድረግ የሚጠይቅ ከሆነ፣ ቻንስለሩ ለተማሪው እና ለወላጅ ለዚህ እርምጃ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው፡፡*

** ማስታወሻ፡- ከላይ የተገለጹት መስፈርቶች ተፈጻሚ የማይሆኑበት ልዩ ምክንያት አለ፤ እርሱም ተማሪው ጋን ፍሪ ስኩልስ አክት ተብሎ የሚታወቀውን ሕግ የጣሰ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ የፌዴራል መንግሥት ሕግ መሠረት አንድ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት የጦር መሣሪያ ይዞ የመጣ መሆኑ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ የጦር መሣሪያ ይዞ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በታች ለሆነ ጊዜ በትምህርት ቤቱ ከመማር ታግዶ እንዲወጣ መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ቻንስለሩ ከትምህርት ቤት የማስወጣቱን መስፈርት ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡*

## በእግድ ሒደት ውስጥ የልጄ መብቶች ምን ምን ናቸው?

በሕጉ መሠረት እርስዎ እና ልጅዎ **በፍትሐዊ ሂደት** የመዳኘት የማግኘት መብት አላችሁ፡፡ ይህም ማለት ልጅዎ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ስለተደረገባቸው ምክንያቶች እና እገዳው ለ6 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ በሚሆን ጊዜ ደግሞ የእገዳው ምክንያት በገለልተኛ 3ኛ ወገን እንዲታይ የማድረግ መብት አላችሁ፡፡ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ተማሪዎች ከዚህ በማስከተል በተዘረዘረው መሠረት ተጨማሪ መብቶች አሏቸው፡-

**በአጠቃላይ ትምህርት ላሉ ተማሪዎች የፍትሐዊ ሂደት መብቶች፡-**

በ DCPS አንድን ተማሪ በይፋ ከትምህርት ቤት ለማገድ የሚከተለውን ሂደት ጠብቆ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ተማሪ የታገደ እንደሆነ፣ ትምህርት ቤቶች የሚከተለውን መፈጸም አለባቸው፡-

- **ተማሪው የአስተዳደር ስብሰባ እድል እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡-** የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት ወይም የእርሳቸው ተወካይ በድንገተኛ ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር (ከዚህ በታች ያለውን ይመልከቱ) እገዳውን ተግባራዊ ከማድረግ በፊት ከተማሪው ጋር ስብሰባ መቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ አስቸኳይ ሁኔታ ካለ ደግሞ እገዳው ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ከሶስት (3) የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስብሰባ መደረግ አለበት፡፡
- **ክስተቱን መመልከት እና አግባብነት ያለውን የሥነ ሥርዓት እርምጃ መወሰን ይገባል፡፡**
- **ከእገዳው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ በሰነድ መያዝ፡፡**
- **የቀረበውን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ሐሳብ በተመለከተ ለወላጅ/ለአሳዳጊ በጽሑፍ ማሳወቅ፡-** በሐሳብነት ስለቀረበው እገዳ ለወላጆች በስልክ ማሳወቅ ይቻላል፡፡ ማናቸውም እገዳ ከተጣለ በ24 ሠዓታት ውስጥ በተረጋገጠ ፖስታ ወይም በእጅ ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ በጽሑፍ የተዘጋጀ ማሳወቂያ መላክ ወይም መስጠት አለበት፡፡
- **የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፡-** ከሁለት (2) ቀናት በላይ እገዳ ከተጣለ፣ ተማሪዎች በእገዳ ላይ ባሉበት ጊዜ ለሚያመልጣቸው ትምህርት የትምህርት ዕቅድ እና የቤት ሥራ ማዕቀፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
- **ዳኝነት፡-** አንድ ተማሪ ለስድስት (6) ቀናት ወይም ከዚያ በላይ የታገደ እንደሆነ ወይም ከትምህርት ቤቱ ከተባረረ በገለልተኛ ዳኛ ጉዳዩ በዳኝነት እንዲታይ መብት ይኖረዋል፡፡

**በድንገተኛ ሁኔታ ስለሚጣል እገዳ**

አንድ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ለተከሰተ ድንገተኛ ሁኔታ አስተዋፅኦ ያደረገ እንደሆነ ከላይ የተገለጸው ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ አካሄድ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በመደበኛ የትምህርት ቀን ወዲያውኑ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል፡፡ ድንገተኛ በሆነ ምክንያት አንድ የጠቅላላ ትምህርት ተማሪ የታገደ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ይህ ተማሪ በትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ የሚባል ስጋት ያስከተለ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ተማሪ የIEP ወይም 504 ዕቅድ ካለው (ወይም ለዚህ ዕቅድ በመመዘን ላይ ካለ) የተማሪው ባሕርይ ቢያንስ ከዚህ የሚከተሉት ማሟላት አለበት፡-

- ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርታዊ ተግባራት የጦር መሣሪያ ይዞ የሚመጣ ከሆነ፤
- ተማሪው በትምህርት ቤት ሳለ ወይም በአንድ የትምህርት ቤት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ሕገወጥ እፆች የሚይዝ ወይም የሚጠቀም ወይም ለመሸጥ የሚሞክር ከሆነ፤ ወይም
- ተማሪው በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ወይም በትምህርት ቤቱ በተዘጋጀ በDCPS ስር በሚገኝ ተግባር ወይም እንቅስቃሴ ሳለ በሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የሚባል አካላዊ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡

### የግላዊ ትምህርት እቅድ(IEP) ወይም የ 504 እቅድ (Plan) ያላቸው እክል ያለባቸው ተማሪዎች ፍትሃዊ ሂደት መብቶች

የዲሲፒኤስ (DCPS) ሠራተኞች፣ ወላጅ እና የግላዊ ትምህርት ዕቅድ (IEP) ቡድን አግባብነት ያላቸው አባላት የተማሪውን የግላዊ ትምህርት እቅድ(IEP)፣ ማናቸውንም የመምህር አስተያየት፣ ማናቸውም በወላጆች የተሰጡ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች እና ሌሎች በተማሪው ማሕደር ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች በማየት ጥያቄ ያስነሳው ባሕርይ ከተማሪው የአካል ጉዳተኝነት ጋር ቀጥተኛ ወይም ሠፊ ግንኙነት ያለው መሆኑን ወይም በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት የተከተለ መሆኑን መወሰን አለባቸው፤ ወይም ይህ ባሕርይ የተከሰተው ዲሲፒኤስ (DCPS) የተቀመጠውን ግላዊ የትምህርት መርሃ-ግብር ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ ከሆነም መታየት አለበት፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት አለ የሚል ውሳኔ ላይ ከተደረሰ፣ DCPS እነዚህን ጉድለቶች ለማረም አፋጣኝ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡ የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች ስለተቀመጠው ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን https://dcps.dc.gov/specialeducation ይመልከቱ፡፡

## እግድ በትምህርት ቤት በመገኘት ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድነው?

በትምህርት ቤት ውስጥ ሳሉ የሚታገዱ ተማሪዎች በትምህርት ላይ እንዳሉ ይቆጠራሉ፡፡ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ሆነው እንዲታገዱ ከተደረጉ ደግሞ ለመቅረታቸው በቂ ምክንያት አላቸው ተብሎ ይወሰዳል፤ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ሆነው ታግደው እንዲቆዩ ከተደረገ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለመቅረት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስረዳት ሰነድ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡

## የልጄን እግድ በተመለከተ የሚያሳስቡኝ ነገሮች አሉ፡፡ በልጄ እግድ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ስለምችልበት ቦታ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው የት ነው?

የዲሲፒኢኤስ (DCPS) የሥነ ሥርዓት አጠባበቅ ፖሊሲዎች በ2018 በተሻሻለውና በወጣው የተማሪዎች ፍትሃዊ ትምህርት የማግኘት (Student Fair Access to School Amendment Act of 2018) ህግ እንዲሁም በዲሲ ማኒሲፓል ሬጉሌሽንስ ምዕራፍ 25 (DC Municipal Regulations Under Chapter 25) ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ወላጆች/አሳዳጊዎች ማንኛውንም እገዳ በመቃወም ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ማስረጃ ማቅረብ እና ምስክሮች እንዲመሰክሩ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የይግባኝ ጥያቄዎች በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

- ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍል (K-5)ላሉ ተማሪዎች ከአንድ (1) - ሶስት (3) ቀናት ለሆነ እግድ፣ ወይም ከ6-12ኛ ላሉ ተማሪዎች ከአንድ (1) - አምስት (5) ቀናት ለሆነ እግድ ይግባኝ የሚሰማው በርዕሰ መምህሩ/ሯ ሲሆን፣ የእግድ ማሳወቂያው በደረሰ በሁለት (2) ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
- ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 5ኛ ክፍል (K-5) ተማሪዎች ከአራት (4) - አምስት (5) ለሆነ እግድ ይግባኝ የሚሰማው በትምህርት ኃላፊ (ኤጁኬሽናል ሱፐርኢንቴንደንት) ነው፡፡
- ከ6-12ኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች ከስድስት (6) - አሥር (10) ቀናት ለሆነ እግድ፣ ወላጆች በገለልተኛ ዳኛ ፊት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ ጉዳዩ በዳኛ ከታየ በኋላ የተጣለ እግድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚፈልግ ወላጅ ካለ፣ ይግባኙን የሚያዩት የቻንስለሩ ተወካይ ናቸው፤ ይግባኙም የመጨረሻው የእግድ ውሳኔ ማሳወቂያ በደረሰ በአምስት (5) ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

የልጅዎን የትምህርት ተጠሪ (Instructional Superintendent ) ለማግኘት እባክዎ https://dcps.dc.gov/page/instructional-superintendents ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

በሁሉም ሁኔታዎች አንድ ተማሪ እና/ወይም ወላጅ ቅሬታ ካላቸው፣ በDCPS ለተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ፍትሐዊ አሠራሮች እንዲኖር እና አፋጣኝ ውሳኔ የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚያመቻቸው ኦፊስ ኦፍ ኢንተግሪቲ ዘንድ ጉዳዩን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከላይ በጽሑፍ ከተቀመጠው ሒደትም በተጨማሪ በስልክም ቢሆን ዘ ኦፊስ ኦፍ ኢንተግሪቲ የሚባለውን መ/ቤት ማግኘት ይቻላል፡፡ እገዛ ለማግኘት እባክዎን በስልክ ቁጥር (202) 939-4913 ይደውሉ ወይም DCPS.cio@k12.dc.gov ይመልከቱ።

# ውጤት አሰጣጥ እና ከክፍል ወደ ክፍል ስለመዘዋወር

## ምልከታ

*መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል በተመለከተ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ግብረ መልስ ከሚሰጡባቸው ወሳኝ ዘዴዎች መካከል የትምህርት ውጤት እና የስኬት ሪፖርት ናቸው፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ አማካኝነት ስኬታማ ለመሆን መውሰድ ያሉባቸውን እርምጃዎች ይገነዘባሉ፡፡ ዲሲፒኢኤስ (DCPS) ለሁሉም ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ወደ ምረቃ በሚያደርጉት ጉዞ ወጥነት ያለው ግብረ መልስ ለመስጠት ሁሌም ዝግጁ ናቸው፡፡*

## ከመዋዕለ-ህጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያለ ልጄ ወደቀጣዩ የክፍል ደረጃ ለመሸጋገር ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሽግግርም ሆነ እገዳ (retention) *ውሳኔ የሚሰጠው በልጅዎ ርዕሰ-መምህር ሲሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግንዛቤ ማስገባት ይኖርበታል፤*

- *ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ለመሸጋገር* ***ሁሉም ተማሪዎች*** *በሙሉው የትምህርት ዓመት ውስጥ* **ከ30 ምክንያት የሌላቸው ቀሪዎች በላይ ቀሪ ሊኖርባቸው አይገባም።**
- **ከቅድመ እስከ መዋዕለ ሕፃናት ያሉ ተማሪዎች፡-** *ከቅድመ እስከ መዋዕለ ሕፃናት ያሉ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ሁኔታ የሚመዘነው በGOLD የምዘና ሥርዓት መሠረት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ከዚህ በሚከተሉት መስኮች የተማሪዎችን የእድገት ሁኔታ ይመዝናል፡- ሒሳብ፣ ማንበብ እና መጻፍ፣ ኮግኒቲቭ፣ ማኅበራዊ/የስሜት፣ ቋንቋ እና አካላዊ እድገት፡፡ ተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ መምህር/ት ማግኘት ይችላሉ፡፡*
- **ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ 5ኛ ክፍል፡-** *ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ መዋዕለ ሕፃናት እንዲሁም እስከ አምስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በዋና ዋና የንባብ/የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ስዕል፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ እና ማኅበራዊ ትምህርት ፕሮፊሸንት ወይም ከፍተኛ ውጤቶች (2፣ 3 ወይም 4) ያገኛሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ መምህር ያገኛሉ፡፡*
- **ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል**፡- *ተማሪዎች በሁሉም ዋና ዋና ትምህርቶች (እንግሊዝኛ፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ እና ማኅበራዊ ትምህርት) ማለፊያ ውጤት ማለትም "D" ወይም ከዚያ በላይ ማግኘት አለባቸው፡፡*

## በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ያለ ልጄ ወደቀጣዩ የክፍል ደረጃ ለመሸጋገር ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

**ከ9 እስከ 11ኛ ክፍል**፡- *ተማሪዎች በእያንዳንዱ ክፍል ስለ ውጤት አደማመርን በሚመለከት በዲሲ ማኒሲፓል ህጎች* (DC Municipal Regulations) *የተቀመጡትን ከክፍል ወደ ክፍል የመዘዋወር መስፈርቶች ሚሟላት አለባቸው፡፡*


- ወደ 10ኛ ክፍል መሸጋገር፤ የ9ኛ ክፍል እንግሊዝኛን ጨምሮ ስድስት (6) ነጥቦች ያገኘ ማንኛውም ተማሪ ወደ 10ኛ ክፍል ለመሸጋገር ብቁ ነው።
- ወደ 11ኛ ክፍል መሸጋገር፤ የ10ኛ ክፍል እንግሊዝኛ እና አልጀብራን ጨምሮ አስራ ሁለት (12) ነጥቦች ያገኘ ማንኛውም ተማሪ ወደ 11ኛ ክፍል ለመሸጋገር ብቁ ነው።
- ወደ 12ኛ ክፍል መሸጋገር፤ የ11ኛ ክፍል እንግሊዝኛን ጨምሮ አስራ ስምንት (18) ነጥቦች ያገኘ ማንኛውም ተማሪ ወደ 12ኛ ክፍል ለመሸጋገር ብቁ ነው።

## ልጄ የማለፊያውን መስፈርት ካላሟላ የበጋ ትምህርት መከታተል ይጠበቅበታል?

አዎ፤ መስፈርቱን ባለሟሟላታቸው እና/ወይም ከ30 በላይ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ቀሪ ያለባቸው ተማሪዎች የበጋ ትምህርት መከታተል ይኖርባቸው ይሆናል። እንዲህ ባለው ሁኔታ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው በኩል የሚነገራቸው ሲሆን የበጋ ትምህርት ምዝገባን በሚመለከትም መረጃ ይሰጣቸዋል። ዲሲፒኤስም (DCPS) አማራጭ የበጋ የማዳበሪያ መርሃግብር ይሰጣል። አስፈላጊ ስለሆነ የበጋ ትምህርት ወይም ስለአማራጭ የበጋ የማዳበሪያ መርሃ-ግብሮች የበለጠ ለመረዳት https://dcps.dc.gov/summer ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

## የልጄን የትምህርት እድገት በሚመለከት እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች በመካከለኛ ጊዜ የትምህርት አቀባበል ውጤት ሪፖርት፣ በሪፖርት ካርድ፣ በወላጅ/አሳዳጊ ስብሰባ እና በሌሎች ማሳወቂያ ዘዴዎች በመደበኛነት ስለ ትምህርት አቀባበል ሁኔታቸው መረጃ ይሰጣል፡፡ የመውደቂያ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች በትምህርት ድ ጋፍ እቅድ እና ወደ ተማሪ ድጋፍ ቡድን በመላክ እገዳ እንዲሰጣቸው ማድረግ ይገባል፡፡




ቤተሰቦች ሶስተኛው የውጤት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት 12 ቀናት ውስጥ ስለ ተማሪው ወደቀጣይ የክፍል ደረጃ የመዘዋወር ሁኔታ ወይም ስለምረቃ በጽሑፍ መረጃ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ ተማሪዎች ወደ ቀጣይ የክፍል ደረጃ የማይዘዋወሩበት ወይም ላይመረቁ የሚችሉበት ሁኔታ ካለ፣ ተማሪው ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲገባ/እንድትገባ ከእናንተ ጋር ቀረብ ብለን እንሠራለን፡ ፡ ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚማሩ ልጆች ወላጆች ስለ ተማሪዎች ውጤት እና በትምህርት ቤት ስለመገኘት በአስፐን በሚገኝ የወላጆች ፖርታል አማካኝነት መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡
ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን ይመልከቱ፡- https://dcps.dc.gov/page/parent-portal.

## ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ውስጥ ልጄ ያመለጠውን/ጣትን የክፍል ስራ ማካካስ ይችላል/ትችላለች?

ተማሪ ከትምህርት ክፍል በሚቀርበት ጊዜ መምህራን ለተማሪዎች ያመለጠውን የክፍል ስራ የማካካስ ዕድል ይሰጣሉ ። በኮርሱ መጀመሪያ ላይ መምህራን ትምህርት ቤት አቀፍ የሆነውን የክፍል ስራን የማካካስ ፖሊሲ በሚመለከት ለተማሪዎች በጽሁፍ መስጠት ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ ት/ቤት ለእያንዳንዱ ያመለጠ ስራ ከአንድ ሙሉ ቀን ያላናሰ ተመጣጣኝ የሆነ የማካካሻ ስራ ማጠናቀቂያ ጊዜ መወሰን ይኖርበታል። መምህራን የማካካሻ ስራን ውጤት ሲሰጡ የአሰራሮችሁን መስፈርቶች መከተል ይኖርባቸዋል።

## ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የልጄ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት መቅረት በልጄ የትምህርት ውጤት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድነው?

በትምህርት ላይ ሁሌ መገኘት ትምህርቱ የሚጠይቀውን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ወሳኝ ነው። ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምሕርቱ ዓይነት ስታንዳርድ መሠረት ያገኙትን ውጤት እንዲያመላክት ከA እስከ F ውጤት ይሰጣቸዋል፡፡ በክፍል መገኘት ትምህርት ለመቅሰም እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ አንድ ተማሪ ከ**30 ቀናት በላይ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ከትምህርት ቤት የቀረ እንደሆነ**፣ ለዚያ የትምህርት ዓይነት የሚሰጠው ውጤት F ይሆናል፡፡ አንድ ተማሪ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ለ10 ቀናት ከትምህርት ቤት ከቀረ፣ ትምህርት ቤቱ ለተማሪው ቤተሰብ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይልካል፡፡ ተማሪው ለ15 ቀናት ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ከቀረ፣ ሌላ ደብዳቤ ወደ ቤተሰብ ይላካል፡፡ ተማሪው በዕለት ተዕለት ትምህርት ላይ መገኘት ካስቸገረው፣ ሊሰጡ ስለሚችሉ ድጋፎች እባክዎን ከመምህሩ/ሯ ወይም ከትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ጋር ይነጋገሩ፡፡

## በልጄ ውጤቶች እና/ወይም የመድገም ውሳኔ ላይ ጥርጣሬዎች ቢኖሩኝ ይግባኝ የማልቱ ሂደት እንዴት ነው?

አንድ ወላጅ/አሳዳጊ እና/ወይም ተማሪ ስለ ውጤት እና/ወይም በድጋሚ ክፍሉን እንዲደገም በተወሰነው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው፣ ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይግባኝ በጽሑፍ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን፣ የይግባኝ ቅጽ ምሳሌ ከዚህ መመሪያ በስተመጨረሻ ተሰጥቷል፡፡

- **በውጤት ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**፡- አንድ ወላጅ ወይም ተማሪ ትክክል አይደለም ወይም ያሳስታል ያሉት የትምህርት ሪኮርድ እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ወላጅ ወይም ተማሪ በማናቸውም የጽሑፍ ፎርም ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ውጤትን የሚመለከት ይግባኝ ውጤቱ በደረሰ በአስር (10) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር መቅረብ አለበት፡፡ ርዕሰ መምህሩም የቀረበውን ይግባኝ ከተመለከቱ በኋላ ውሳኔያቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተማሪ በርዕሱ መምህሩ/ሯ ውሳኔ በደረሳቸው በአምስት (5) የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ ለትምህርት ኃላፊው ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
- **በመቅረት ምክንያት በመውደቅ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ**፡- ከ30 ቀናት በላይ በመቅረት ምክንያት እንዲወድቅ የተደረገ ተማሪ ወላጅ ወይም ተማሪው ራሱ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት ወይም ለቻንስለሩ ተወካይ ውጤቱ በደረሰ በእር (10) የትምህርት ቀናት ይግባኝ ይችላሉ፡፡ የይግባኝ ጉባዔ ይግባኙን ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ተማሪው ወይም ወላጅ ውሳኔው በደረሳቸው በአስር (10) ቀናት ጊዜ ውስጥ በጉባዔው ውሳኔ ላይ ያላቸውን ይግባኝ ለቻንስለር በጽሑፍ ወደ FAGrade.CentralAppeal@dc.gov በመላክ ማቅረብ ይችላሉ።
- **ክፍል በመድገም ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**፡- አንድ ተማሪ አንድን ክፍል ደግሞ እንዲማር በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ወላጅ ወይም ተማሪ በማናቸውም የጽሑፍ ፎርም ለትምህርት ኃላፊው ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የትምህርት ኃላፊው የቀረበውን ይግባኝ መርምረው ውሳኔያቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡

የልጅዎ የትምህርት ተጠሪ (Instructional Superintendent) ማን እንደሆነ ለማወቅ እባክዎ https://dcps.dc.gov/page/instructional-superintendents ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

በሁሉም ሁኔታዎች አንድ ተማሪ እና/ወይም ወላጅ ቅሬታ ካላቸው፣ ጉዳዮች በአፋጣኝ እንዲፈቱ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ፍትሐዊ አሰራርን በማበረታታት ለሁሉም DCPS ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ለሚሰጠው ለኦፊስ ኦፍ ኢንተግሪቲ ማመልከት ይችላሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሂደቶች በተጨማሪ፣ ጥያቄዎች ለኦፊስ ኦፍ ኢንተግሪቲ በስልክ አማካኝነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እገዛ ለማግኘት እባክዎን በ (202) 939-4913 ይደውሉ ወይም DCPS.cio@k12.dc.gov ይመልከቱ፡፡

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውጤትን ማሻሻል

## ምልከታ

ውጤትን ማሻሻል (credit recovery) ዋነኛ ትኩረቱ ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ፤ የትምህርቱን ይዘት በበለጠ እንዲረዱ፤ እና ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ ሆነው እንዲጨርሱ መርዳት ነው። በውጤትን ማሻሻል መርሃ-ግብር ውስጥ የታቀፉ ተማሪዎች የዲሲፒኤስ (DCPS) ካሪኩለምን እና ደረጃ በጠበቁ ፈታኝ፤ ግላዊ፤ እና በየትኛውም ቦታ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በሚያስችላቸው ትምህርቶች ውስጥ ይሳተፋሉ። እነዚህ የትምህርት ዓይነቶች ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ወቅታቸው በደንብ ባላወቋቸው የትምህርት ይዘቶች እንደገና እንዲሳተፉ ያስችሏቸዋል።

## ልጄ ውጤት ማሻሻያ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ነው?

ለውጤት ማሻሻያ ብቁ የሚሆኑት በመጀመሪያ የትምህርት ጊዜያቸው የትምህርት ዓይነቱን ወስደው በትምህርት ዓይነቱ ያላለፉ የሁለተኛ ደራጃ ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ተማሪዎች መደበኛውን የትምህርት እየወሰዱ እያሉ ወይም ደግሞ በመደበኛው የትምህርት ዓይነት ፋንታ የውጤት ማሻሻያ አይወስዱም። በውጤት ማሻሻያ መርሃግብር በመመዝገብ ሂደት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አማካሪያቸው (guidance counselor) ድጋፍ ያገኛሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው ውጤት ማሻሻያ መርሃግብር ውስጥ እየተሳተፈ ስለመሆኑ ሊነገራቸው ይገባል። ተማሪዎ በፊት በወደቀበት ትምህርት ውጤት ለማግኘት በውጤት ማሻሻያ ውስጥ መመዝገብ ካስፈለገው የተማሪዎን አማራጮች በሚመለከት ከትምህርት ቤቱ አማካሪ (guidance counselor) ጋር ይወያዩ።

## ውጤትን ለማሻሻል ልጄ የት መመዝገብ ይችላል?

አናኮስቲያ (Anacostia)፤ ባሉ (Ballou)፤ ካርዶዞ (Cardozo)፤ ኩሌጅ (Coolidge)፤ ኮሎምቢያ ሃይትስ ኢዱቻሽን ካምፓስ (Columbia Heights Education Campus)፤ ደንባር (Dunbar)፤ ኢስተርን (Eastern)፤ ፌልፕስ (Phelps)፤ ሩዝቬልት (Roosevelt)፤ ሮን ብራውን (Ron Brown)፤ ዊልሰን (Wilson)፤ እና ኤች ዲ ዉድሰን (H.D. Woodson) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የውጤት ማሻሻያ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። በውጤት ማሻሻያ ለመሳተፍ ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ቤት ወይም በሌላ ትምህርት ቤት መመዝገብ ይችላሉ።

## ልጄ የውጤት ማሻሻያ ትምህርትን ሲከታተል በትምህርት ላይ የመገኘት መስፈርቶቹ ምንድናቸው?

ትምህርቶቹ የሚሰጡት ከተለመደው የትምህርት ሰዓት ውጪ በመሆኑ ምክንያት መምህራን እና ተማሪዎች በሳምንት ሶስት ወይም አራት ወይም አምስት ቀናት በአካል ትምህርት የሚከታተሉበትን መርሃ ግብር ያወጣሉ። በአካል ትምህርት ላይ ከመገኘት በተጨማሪ ተማሪዎች የቤት ስራ እና የኦንላይን የትምህርት ስራዎች (online coursework) ይጠበቅባቸዋል። ተቀባይነት በሌለው ምክንያት በአካል መገኘት ከነበረባቸው ቀናት 18 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከቀሩ ከትምህርት ክፍሉ የሚለቁ ሲሆን (withdrawn) “W” የሚል ውጤት ያገኛሉ።

## ምን አይነት ውጤቶች ናቸው ልጄ የውጤት ማሻሻያ ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ማጠናቀቁን የሚያሳዩት?

በትምህርት ዓይነቱ “D” ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ ተማሪዎች የውጤት ማሻሻያውን በተሳካ ሁኔታ የሚያልፉ ሲሆን በትምህርት ዓይነቱም ውጤት ያገኛሉ። ከ 18 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ክፍሉ የቀሩ ወይም ደግሞ በትምህርት ዓይነቱ “D” ወይም ከዚያ በላይ ያላገኙ ተማሪዎች "W" የሚል ውጤት ያገኛሉ። የውጤት ማሻሻያ ኮርስ ውጤቶች የተማሪዎች ውጤት ማሳያ ካርዶች ላይ (transcript) የሚመለከቱትን መደበኛ የትምህርት ውጤቶች አይተካም። ሁሉም ውጤቶች ተማሪው ውጤት ማሳያ ላይ የሚመለከቱ ሲሆን የተማሪዎች አማካይ ውጤት ላይ ይታያሉ።

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምረቃ

## ምልከታ

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ሁሉም ተማሪዎች በኮሌጅ፣ በሙያቸው እና በሕይወት ስኬታማ እንዲሆኑ ከልብ ይሰራል፡፡ ለዚህም ሁሉም ተማሪዎች ለምረቃ ብቁ ለመሆን የሚያበቋቸውን ስታንዳርዶች ማስቀመጥ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ ተማሪዎችን ለስኬት ብቁ ለማድረግ በሚጫወቷቸው ቁልፍ ሚናዎች አንጻር ተጠያቂ እንደሆኑ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ DCPS ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቁርጠኛ አቋም አለው፡-

- ከሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት መጠበቅ እና ሁሉም ምሩቆች ዲፕሎማ ያገኙት በእርግጥም ስለሚገባቸው መሆኑን ማመናቸውን ማረጋገጥ፤
- ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ወደ ምረቃ በሚያደርጉት ጉዞ ለስኬታማነት የሚያስፈልጋቸውን እገዛ እያገኙ እንዲቲጉ ማበርታት፤ እና
- በጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ግልጽ የሆኑ ፖሊሲዎች ማስቀመጥ፡፡

## የ ዲሲፒኤስ (DCPS) የምረቃ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

የ ዲሲፒኤስን (DCPS) ዲፕሎማ ለማግኘት፣ ሁሉም ተማሪዎች 24.0 ክሬዲት ማግኘት እና የ100 ሰዓት የማኅበራዊ አገልግሎት ሰዓታት ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡

| የትምህርት ዓይነት | ክሬዲት (ካርኒጌ ዩኒት -Carnegie Unit) |
|---|---|
| እንግሊዝኛ | 4.0 ክሬዲት |
| ሒሳብ (አልጀብራ I፣ ጂኦሜትሪ፣ አልጀብራ II) | 4.0 ክሬዲት |
| ሳይንስ (ሦስት የላብራቶሪ ሳይንሶችን ማካተት አለበት) | 4.0 ክሬዲት |
| ማኅበራዊ ሳይንስ (የዓለም ታሪክ 1 እና 2፣ የዩናይትድ ስቴትስ ታሪክ እና የኮሉምቢያ ዲስትሪክት ታሪክ መካተት አለባቸው) | 4.0 ክሬዲት |
| የዓለም ቋንቋ | 2.0 ክሬዲት |
| ስዕል | 0.5 ክሬዲት |
| ሙዚቃ | 0.5 ክሬዲት |
| ጤና እና የአካል ብቃት ትምህርት | 1.5 ክሬዲት |
| አማራጮች | 3.5 ክሬዲት |
| ድምር | 24.0 **ክሬዲት** |

- ከሦስት (3) የላብራቶሪ ሳይንስ ክፍል መካከል አንዱ (1) የባዮሎጂ ትምህርት አካል መሆን አለበት፡፡
- ለምረቃ ከሚያስፈልጉ ሃያ አራት (24) ካርኒጌ ዩኒቶች (Carnegie Unit) መካከል ቢያንስ ሁለቱ (2) የኮሌጅ ደረጃ ወይም የሙያ ዝግጅት (CLCP) ትምህርቶች፣ ለምሳሌ የከፍተኛ ደረጃ ምደባ ወይም ሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት መሆን አለባቸው፡፡ ተማሪዎች እና ወላጆች ስለሚሰጡ ትምህርት ዓይነቶች ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት የትምህርት ቤታቸውን አማካሪ ማነጋገር ይችላሉ፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች ከአስረኛ (10ኛ) ክፍል ሳያልፍ የአልጀብራ I ትምህርት መማር አለባቸው፡፡
- ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማታ ፕሮግራም ዲፕሎማ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የጤና እና የአካል ብቃት ትምህርት 1.5 ክሬዲት መውሰድ አይጠበቅባቸውም፡፡
- ሁሉም ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት የ100 ሰዓታት የማኅበራዊ አገልግሎት ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡

*ማስታወሻ፤ በልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (Specialized High Schools) ወይም ልዩ መርሃግብር ባላቸው ትምህርት ቤቶች የተመዘገቡ ተማሪዎች (ለምሳሌ ኢስተርን አለም አቀፍ ዲግሪ መርሃ-ግብር (Eastern International Baccalaureate Program) ከዲሲፒኤስ 24 ክሬዲቶች DCPS 24 credits) የበለጠ የመመረቂያ ይጠበቅባቸዋል።*

**የ ግላዊ ትምህርት መርሃግብር (IEP) ማጠናቀቂያ የምሥክር ወረቀት**

የአካል ጉዳት ያለባቸው እና የIEP ግቦችን ያሳኩ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቅ ችለው ነገር ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ስታንዳርዶች ማሟላት ያልቻሉ ተማሪዎች የIEP ማጠናቀቂያ የምሥክር ወረቀት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ በhttps://dcps.dc.gov/specialeducation ማግኘት ይቻላል፡፡

## ከሌላ ት/ቤት የተገኙ ተላላፊ ውጤቶች እንዴት ነው የሚገመገሙት

ተማሪው የዲሲ ቻርተር ት/ቤቶችን፤ ሌላ ስቴት ያሉ ት/ቤቶችን፤ የኤምባሲ ት/ቤቶችን፤ የቤት ውስጥ ትምህርትን እና ከአሜሪካ ውጪ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ከዲሲፒኤስ (DCPS) ውጪ ከሆነ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውጤት ሲያመጣ ዲሲፒኤስ (DCPS) የተማሪውን የውጤት ካርድ (transcript) የትኞቹ ውጤቶች ለዲሲፒኤስ (DCPS) ዲፕሎማ እንደሚያበቁ ለመወሰን መገምገም አለበት። ዲሲፒኤስ (DCPS) የተረጋገጡ የውጤት ካርዶችን (official transcripts) ብቻ የሚገመግም ሲሆን ሁሉንም ውጤቶች ላይቀበል ይችላል። ዲሲፒኤስ (DCPS) የተገኘው ውጤት ተወባይነት ካለው እና ባለበት ግዛት ታዋቂ ከሆነ ት/ቤት የተገኘ መሆኑን ያረጋግጣል ወይም ደግሞ በዲሲፒኤስ (DCPS) ተቀባይነት የሚኖራቸውን ሌሎች መስፈርቶች ይወስናል።
ለልጄ አማካይ የውጤት ነጥቦች (GPAs) እንዴት ነው የሚሰሉት?

## ለልጄ አማካይ የውጤት ነጥቦች (GPAs) እንዴት ነው የሚሰሉት?

አማካይ የደረጃ ነጥብ (GPA) የሚሰላው የሁሉንም ብቁ የትምህርት ክፍሎች አማካይ ውጤት በማስላት ነው። ለሁሉም የዲሲፒኤስ (DCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አማካይ የክፍል ነጥቦች ተከታታይነት ባለው ሁኔታ፤ ትክክለኛ እና እኩል በሆነ ሁኔታ መሰላቱን ለማረጋገጥ ሁሉም አማካይ የክፍል ደረጃ ነጥቦች (GPAs) እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃዎች የክልሉን የተማሪ መረጃ አሰራር ሂደት በመከተል ማእከላዊ በሆነ ሁኔታ ይሰላሉ። ዲሲፒኤስ (DCPS) የሚከተሉትን ሶስት ዓይነት አማካይ የክፍል ደረጃ ነጥቦች (GPAs) ይተገብራል፤

- **አጠቃላይ ድምር አማካይ የክፍል ደረጃ ነጥብ (GPA)፤** በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተወሰዱ የትምህርት ዓይነቶችን ማጠቃለያ ነጥቦች ያካትታል። ውጤቶች በተማሪ የውጤት መመዝገቢያዎች (student transcripts) የሚያዙ ሲሆን ለክፍል ደረጃ ጥቅም ላይ ይውላሉ።
- **የፈረቃ አማካይ ነጥብ (Term Grade Average)፤** ተማሪው በወቅቱ እየወሰደ ያለውን ኮርሶች ነጥቦች ጨምሮ የወቅቱን ነጥቦች ብቻ ያካትታል።ውጤቶቹ የተማሪ ውጤት መመዝገቢያዎች (transcripts) አይሰፍሩም ነገር ግን የውጤት መመዝገቢያ ካርድ but do appear on the (report card) ላይ ይታያሉ። ውጤቶች አጠቃላይ ክብ ለመስጠት ዓላማዎች ይውላሉ።
- **ዓመታዊ አማካይ የደረጃ ነጥብ (Year Grade Average)፤** በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ የተገኙ ማጠቃለያ ነጥቦችን ብቻ ያካትታል። ከ1-3 ባሉ ፈረቃዎች በተማሪው እና በትምህርት ቤቱ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በመመርኮዝ ይህ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል። ውጤቶቹ በውጤት ካርዱ ላይ (report card) በየፈረቃው በአዲስ መልክ ይመዘገባሉ።


በዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤቶች የተመዘገቡ የሁሉም ተማሪዎች አማካይ አጠቃላይ ድምር የክፍል ደረጃ ነጥብ፤ የፈረቃ አማካይ ነጥብ እና ዓመታዊ አማካይ የደረጃ ነጥብ F ን ጨምሮ ሁሉንም የተገኙ ውጤቶች ያካትታል። ተማሪው አንድን የትምህርት ዓይነት ደግሞ የወሰደ እንደሆነ እነዚያ ነጥቦች በፊት የተገኙትን ነጥቦች የማይተኩ ሲሆን በተማሪው አጠቃላይ ነጥብ (cumulative GPA) ውስጥ የሚካተቱ ይሆናሉ። . በተራዘመ የትምህርት መርሃግብሮች ማለትም በበጋ ትምህርት፤ ስቴይ ትምህርት (STAY schoo) እና በምሽት የውጤት ማሻሻያ ትምህርቶች የተገኙ ነጥቦች በመደበኛው የትምህርት ዓመት ከሚሰጡ ኮርሶች ጋር አንድ ዓይነት እውቅና እና (GPA) ይኖራቸዋል።

## ልጄ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰዓትን የት ማጠናቀቅ ይችላል?

የ100 ሰዓታት የማኅበረሰብ አገልግሎት ከክፍያ ነጻ የሆነ ለማኅበረሰቡ አገልግሎት በበጎ ፈቃደኝነት የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፣ ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት [501(c)(3)]፣ በትምህርት ቤቶች፣ በፌዴራል ወይም በአካባቢ ኤጀንሲዎች ወይም በሌሎች ድርጅቶች ዘንድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ አገልግሎት ተማሪው በክፍል ውስጥ ሊገኝ በሚገባው ጊዜ ሊካሄድ አይችልም፡፡ ማኅበራዊ አገልግሎቱ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ፣ አገልግሎቱ መዋቅራዊ እና በክትትል የሚካሄድ መሆን አለበት፡፡ አገልግሎቱ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መሆን አይችልም፡፡ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው በሚሰጥ ፈቃድ ከ8ኛ ክፍል ጀምረው የማኅበራዊ አገልግሎት ሰዓታቱን ማጠራቀም ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ከ9ኛ ክፍል በፊት ቢበዛ 25 የአገልግሎት ሰዓታት ማጠራቀም ይችላሉ፡፡

## ልጄ ለመመረቅ፤ ለኮሌጅ፤ እና ለስራ የሚያደርጋቸውን ሂደቶች እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የዲሲፒኤስን (DCPS) በተማሪው መረጃ እና ጥረት ላይ የተመረኮዘ ግላዊ የሆነ የመመረቅ፤ የኮሌጅ እና የስራ መምሪያ በየዓመቱ ያገኛሉ።መምሪያው እያንዳንዱ ተማሪ ወደ ምረቃ ስለሚያደርገው ዕድገት እንዲሁም ኮሌጅን እና የስራ እድሎችን በሚመለከት እና ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ግንዛቤ ያስጨብጣል። ማምሪያው የተማሪውን እድገት በሚመለከት ግልጽ የሆነ መረጃን ለመስጠት እና ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፤ ከትምህርት ቤታቸው ጋር በመተባበር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም ሆነ ከዚያ በላይ ስኬታማ የመሆኛ መንገዶችን መፍጠር እንዲችሉ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።



# የመቅረትን ምክንያት ማብራሪያ መልዕክት

እባክዎን የልጅን ______________________________________________ (ስም) የመቅረት ምክንያት ይቀበሉ፡

ልጁ በ__________________________________________ (ቀሪ የሆነበት/ችበት ቀን (ቀናት) ከትምህርት ቤት ቀርቷል/ቀርታለች፤ ምክንያቶቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡-

*እባክዎ ልጅዎ ከትምህርት ቤት የቀረበትን/የቀረችበትን ምክንያት ይምረጡ (አስፈላጊ)፡-*

- ❑ **በተማሪ ሕመም** (በአንድ የትምህርት ተርም ለ5 ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናት ቀሪ የሐኪም ማስረጃ ያስፈልጋል)
- ❑ **የአካላዊ/የጥርስ ሕክምና ቀጠሮ** (እባክዎን በሐኪም የተሰጠ ማስረጃ ያቅርቡ)
- ❑ **የተማሪ ፍርድ ቤት ቀጠሮ** (እባክዎን ተማሪው/ዋ በፍርድ ቤት መገኘቱን/ቷን የሚያሳይ ማስረጃ ያቅርቡ)
- ❑ **ኃይማኖታዊ በዓል** (እባክዎን በዓሉን/ዝግጅቱን ከዚህ በታች ይዘርዝሩ)
- ❑ **የቤተሰብ አባል ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**
- ❑ **ሌላ** ("ሌላ" የሚለውን ከመረጡ፣ እባክዎን ዝርዝር መረጃ ይስጡ፡፡ በዲሲፒኤስ (DCPS) ፖሊሲ ተቀባይነት ያላቸው የመቅረት ምክንያቶች የተወሰኑ ብቻ መሆናቸውን ይገንዘቡ፡፡)

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በአንድ የትምህርት ተርም ለ5 ወይም ከዚያ በላይ በድምሩ አንድ ተማሪ ለማንኛቸውም ምክንያት ከቀረ፡ ይቅርታ እንዲደረግለት ከወላጅ/ከአሳዳጊ ደብዳቤ ከማምጣቱ በተጨማሪ ሌሎች ደጋፊ መረጃዎችን ማቅረብ የግድ ይላል፡፡

የወላጅ ስም (እባክዎን ይጻፉ)፦ ______________________________________

የወላጅ ፊርማ፡- ______________________________________

የወላጅ ስልክ ቁጥር፡- ______________________________________

የዛሬው ዕለት*:- ______________________________________

***የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሕግ በወላጆች/አሳዳጊዎች የተጻፉ የመቅረት ምክንያት ደብዳቤዎች ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት በተመለሰ/ች በአምስት (5) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡**

*ማስታወሻ፡- ይህ ናሙና ቅጽ ነው፡፡ ወላጆች ልጃቸው ከትምህርት ቤት የቀረበትን/ችበት ምክንያት ለመግለጽ ሌሎች የጽሑፍ ፎርሞች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡*

# የይግባኝ ቅጽ

ቀን፡- ____________________

የተማሪው/ዋ ስም፡- ____________________

የተማሪ መታወቂያ፡- ____________________

ትምህርት ቤት፡- ____________________

የወላጅ ስም፡- ____________________

የወላጅ አድራሻ፡- ____________________

**የይግባኙ ምክንያት፡-**

- ❑ የቀሪ ሪኮርድ
- ❑ ውጤት ወይም ማርክ፣ በመቅረት ምክንያት መውደቅን አካትቶ
- ❑ ሥነ ሥርዓት
- ❑ የመድገም ወይም ከክፍል ክፍል የመዛዋወር ውሳኔ

እባክዎን ይግባኝዎን አስመልክቶ መረጃ ይስጡ፡፡

____________________

____________________

____________________

____________________

*አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ ያያይዙ፡፡*

*ማስታወሻ፡- ይህ ናሙና ቅጽ ነው፡፡ ወላጆች ለልጃቸው ይግባኝ ሌላ የጽሑፍ ፎርም መጠቀም ወይም በስልክ ቁጥር (202) 939-4913 በመደወል እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፡፡*

ለትምህርት ቤቱ የደረሰበት ቀን እና የተቀበሉት ሠራተኛ ስም፡- ____________________

# እኛን ይገናኙ

**ድረ ገጽ፤** www.dcps.dc.gov
**Twitter/Facebook/Instagram:** @dcpublicschools
**አድራሻ፤** 1200 First Street, NE, Washington, DC 20002
**ስልክ፤** 202-442-5885

## የታማኝነት ቢሮ

DCPS (የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች) እያንዳንዱን ተማሪ በዕኩልነት፤ በላቅነት፤ በግልጽነት፤ ተጠያቂነት በተሞላው ዘርፍ ለማስተናገድ ዝግጁ ነው፡፡ የታማኝነት ቢሮ፤

- ከተማሪዎች፤ ከቤተሰቦች፤ ከሰራተኞች፤ እና ከማህበረሰብ አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ማግኛ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ግልጋሎት በሚሰጣቸው አካላት ለሚነሱ አሳሳቢ ጉዳዮች ተገቢ የሆነውን መረጃ በመገምገም እርምጃ ይወስዳል፤ ውዝግብንም ለማስተናገድ ተገቢ ሲሆን የውስጥ ኦዲት እና ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
- የ DCPS ፓሊሲዎች ደረጃን ያሳውቃል እናም የትምህርት ፓሊሲ እና ደንብ መጠበቁንም ያረጋግጣል፡፡

ስለ ታማኝነት ቢሮ በተጨማሪ ለማወቅ፤ እባክዎን ይጎብኙ https://dcps.dc.gov/page/office-integrity.

ድጋፍ ለማግኘት እባክዎትን ይገናኙን በ (202) 939-4913 ወይም DCPS.cio@k12.dc.gov

## ፓሊሲዎች

ሁሉንም የ DCPS ፓሊሲዎች ለማግኘት፤ እባክዎትን ይጎብኙ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.